# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

جبهة تحرير أورومـــو

Gaafa: 28-04-2012 stm تاريخ
Date:

Lakk.: 008/-abo/2012 رقم
No.:

## *የሙስሊሙ ህብረተሰብ የመብት ጥያቄ የጸረ ወያኔ ትግሉ ኣካል ነው*
## *የኦሮሞ ነፃነት ግንባር መግለጫ*

*እለተ ኣርብ ሚያዝያ 20 ቀን 2012 በመቶዎች የሚቆጠሩ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ኣባላት “የ
ሃይማኖት መብታችን ይከበር” በማለት በፊንፊኔ ከተማ ጸረ ወያኔ መንግስት ሰላማዊ ሰልፍ ኣ
ካሂደዋል። ይህ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ጥያቄም የሃይማኖታዊ መብት ጥያቄ ነው። የወያኔ መን
ግስት ህብረተሰቡ እስከ ዛሬ ድረስ የሚከተለውን የሃይማኖት ስርኣትና ህግጋት በመተላለፍ ኣ
ብደላ ኣል ሃበሽ በተባሉ ግለሰብ ኣማካኝነት ኣዲስ ያመጣውን ኣል ኣህባሽ የተሰኘ ሃይማኖታዊ
ኣስተምህሮት ካልተቀበላችሁ እያለ በማስገደድ ላይ ነው። በቁጥር ኣናሳ የሆኑትን የመጤው ኣል
ኣህባሽ ኣስተምህሮት ሰባኪዎችን በሁሉም ዝርፍ እየደገፈ ሲያበረታታ መንግስት በሃይማኖታችን
የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት የለበትም ያሉትን ብዙሃኑን የእስልምና ተከታዮችን ደግሞ ማስ
ፈራራትን ተያይዙኣል።*

*የወያኔው ኣምባገነናዊ ስርኣት ከተለያዩ የሃገሪቷ ብሄር ብሄረሰቦች መሃል ሆድ ኣደሮችን እየ
መለመለ በመሳሪያነት እንደሚጠቀምባቸው ሁሉ በተለያዩ ሃይማኖቶች ጣልቃም እጁን ኣስገብቶ
ለመቆጣጠር ተመሳሳይ ስልቶችን ይከተላል። ስርኣቱን የሚደግፉ ካድሬዎችን በሃይማኖት ኣባት
ነት እየሾመ በነሱ በኩል ሁሉንም ሃይማኖቶች የፖለቲካ መሳሪያው ለማድረግ በጥረት ላይ መሆ
ኑ ግልጽ ነው። የእስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባኤ የሚባለው ኣካልም በዚሁ መልኩ የሃይማኖት
ተቋዋም መሆኑን እስኪዘነጋ ድረስ የወያኔ መንግስት ተለጣፊ ሆኖ በማገልገል የሃይማኖቱን
መብቶች እየሸረፈና እያስሸረፈ ነው በማለት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በሃይለኛው እየነቀፉት
ናቸው።*

*ባሁኑ ጊዜ የወያኔ ስርኣት የተያያዘውን ሃይማኖታዊውን ህግጋት የሚጻረር ቅስቀሳ የተቃወሙ የ
እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የተለያዩ ጠላታዊ ስሞች እየተለጠፉባቸው በጭፍን እየተወነጀሉ
መሆኑን ዘገባዎች ያስረዳሉ። በብሄር ማንነታቸው ኦሮሞ የሆኑት ኦነግ እየተባሉ ይዋከባሉ ይታ
ሰራሉ። ሌሎችም የዘር ማንነታቸው እየታየ የብሄራቸው ድርጅት ስም እየተለጠፈባቸው ይ
ሳደዳሉ። ብሄራቸው ያልታወቀ የሃይማኖቱ ተከታዮች ደግሞ ኣል ቃይዳ የሚል ስም እየተ
ሰጣቸው በሽብርተኛነት እንዲታዩ ይደረጋል። የወያኔ መንግስት ባለፉት ስርኣቶች ወደ ዳር
ሲገፉ የኖሩትን እንደ እስላም ያሉ ሃይማኖቶች መብት ዛሬ ተከብሯል፣ የሁሉም ሃይማኖቶች እ
ኩልነት ተረጋግጧል እያለ ይደሰኩራል። በትርጉም ኣልባው ህገ መንግስቱ ላይም “መንግስት
በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ኣይገባም፣ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ ኣይገባም” በማለት
ለስሙ ፅፏል። ይሁን እንጂ ስርኣቱ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲን የሚከተል በመሆኑ በህገ መንግስቱ
ላይ የጻፈውን ይህንን ህግ ተግባራዊ ማድረግ ኣልቻለም። ባሁኑ ጊዜ የተከተለው ስትራቴጂም
በሃይማኖቶች ጉዳይ በስፋት እጁን እያስገባ በተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ብቻ ሳይሆን
ኣንድን ሃይማኖት በሚከተሉ ምእመናን መካከል ሳይቀር የግጭት እሳት ለመጫር ማሴር
ሆኗል። በተለይም ሰሞኑን በኣርሲ ዞን በኦሮሞ ተወላጅ ሙስሊሞች ላይ የተፈጸመው የግድያ
ተግባር እጅግ የሚዘገንን ኣደገኛ የትንኮሳ እርምጃ ነው።*

*ምንም ኣይነት መንግስታዊ ሃላፊነት የማይሰማው ይህ ስርኣት በእስልምናና ክርስትና ሃይማኖት
ተከታዮች መካከል በተለያዩ ጊዜያት በጫራቸው ግጭቶች የበርካታ ዜጎች ህይወት እንዲጠፉና*

P. O. Box 6973 Asmara, Eritrea |Tel 2911 153848 | E-mail abamilki@gemel.com.er *www.oromoliberationfront.org*

ሃብት ንብረት እንዲወድም ምክንያት መሆኑ አይዘነጋም። በክርስትና ሃይማኖት ዘንድ በተለያዩ አብያተ ክርስትያናት መካከል ያሉትን መጠነኛ ልዩነቶችን ለፖለቲካ ኣላማው ማሳኪያ በመጠቀም ይበልጥ ማለያየትና የእምነቱን ተከታዮችም እስከማናቆር ከመሄድ የተቆጠበበት ጊዜ የለም። ከቤተ ክርስትያናቱ መካከል የኦሮሞ ተወላጆች የሚበዙበትን ወዲያው የኦነግ መሰባሰቢያ ተቋዋም የሚል ስም እየለጠፈበት ሌሎችን ያነሳሳበታል። የዋቀፋና እምነት ተከታዮች ደግሞ ሙሉ በሙሉ ኦሮሞ በመሆናቸው ብቻ በኦነግ ደጋፊነት ስም እየተወነጀሉ መዋከብና ኣንድ ሃይማኖት ሊኖሩት የሚገባቸውን መብቶች መነፈግ እድላቸው ሆኗል። ይህ ሁሉ በኣንድ ላይ ተደምሮ የሚያረጋግጠው ወያኔ ኣስ ተዳድራቸዋለሁ ለሚላቸው ህዝቦች ምንም ኣይነት ክብር የሌለውና ሁል ጊዜ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ልዩነቶችን እያራገበ ግጭት በመጫር የስልጣን እድሜውን ማራዘም የሚፈልግ ስርኣት መሆኑን ነው።

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የወያኔ መንግስት በማናቸውም ሃይማኖቶች መሃል እጁን እያስ ገባ ምእመናኑን እርስ በርስ ለማቃቃር የሚያደርገውን ጥረትና የሚፈፅማቸውን የ ሃይማኖት መብት ረገጣዎች በጽኑ ያወግዛል። ኦነግ ሁሉንም ሃይማኖቶች በኣንድ ኣይን የሚመለከትና ለኣንዱ ኣዳልቶ ሌላውን ወደ ዳር በመግፋት የማያምን ድርጅት በመሆኑ የኣንድ ሃይማኖት መብቶች ኣገር ኣስተዳድራለሁ በሚል መንግስት ሲረገጥ እያየ ዝም ብሎ ማለፍ ኣይችልም። ማንኛውም ብሄርም ሆነ የማንኛውም ሃይማኖት ተከታይ ህብረተሰብ የብሄር ወይም የሃይማኖቱን መብቶች ለማስከበር የሚያደርገው ትግል ፍትሃዊ ትግል ነው። በኢትዮጵያ በኣምባገነኑ የመለስ ዜናዊ መንግስት ላይ የሚካሄደው ዘርፈ ብዙ ትግልም ይህንን ኣይነት ትግል ያካትታል። ባሁኑ ወቅት ሙስሊሙ ህብረተ ሰብ በስፋት እያሰማ ያለው የመብት ጥያቄም የዚሁ ምሳሌ በመሆኑ የፀረ ወያኔ ትግሉ ኣካል ነው ብለን እናምናለን።

ማንኛውም ሃይማኖት ለማንኛውም ኣይነት የፖለቲካ ኣላማ ማሳኪያ መዋል እንደሌለበት ሁሉ ማንኛውም የፖለቲካ ኣላማም ሃይማኖትን መሳሪያው ኣድርጎ መንቀሳቀስ የለበትም እንላለን። ማንኛውም መንግስት ህገመንግስቱን ኣለ ኣግባብ በመጠቀም ማንኛውንም ሃይማኖት መጋፋት ኣይኖርበትም የሚለው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ኣቋዋም ነው። ስለሆ ነም የወያኔ ህወሃት መንግስት ባሁኑ ጊዜ በእስልምና ሃይማኖት ጉዳይ ኣጁን እያስገባ የሃይማኖቱ ተከታዮችን መብት እየተጋፋ የፖለቲካ ስርኣቱን እንዲያመልኩለት ለማስ ገደድ የተያያዘውን ጥረት ባስቸኩዋይ እንዲያቆም የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ጥሪ ያስ ተላልፋል። የመለስ ዜናዊ መንግስት ይህንን የከፋ ተግባር በጊዜ ካልገታ ከሃይማኖት ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ነገ በዚያች ሃገር ሊባባስ ለሚችለው ማንኛውም ኣይነት ኣደጋ ተጠያቂ መሆኑን ማስገንዘብ እንወዳለን።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር

ሚያዝያ 28, 2012